የኅብረተሰብ ክፍል ተፈጥረው የነበሩት ብዥታዎች ከሞላ ጎደል ተወግደዋል፡ ሕዝቡ ጠላቱን በውል እየለየ መጥቷልም። እንገቱን ደፍቶ "ቢጭኑት እህያ ቢጋልቡት ፈረስ" ሆኖ ኑሮን መግፋት ሁኔታዎቹን እያባባሰብት በመምጣት ላይ መሆኑን ደግሞ በተጨባጩ እያየ ነው። የፋሽስቱ ፀረ-ሕዝብ እርምጃዎች የሁሉንም የሕዝብ ወገን ደሳሳ ጎጆ፥ የሁሉንም መሸሸጊያ ጎሬ፥ የሁሉንም ፍላጎትና ሕይወት እያመሰቃቀለ ነው። እያንዳንዱ አሳቢ ዜጋ "ከዚህ የባሰ ምን ሊመጣብኝ ነው" ብሎ የሚጠይቅበት ሁኔታ ከተፈጠረ ውሎ አድሯል። መፍዘዝ፥ መደንዘዝም አልፈየደ፤ የራስን ነፍስ ብቻ በተናጠል ለማዳን መሞከር የሀገር የወገን ፍቅር ላለው የሕሊና እረፍት አልሰጠ፤ የካቲት መጥቶ ባለፈ ቁጥር በሚያስታውሰን ሁሉ ስውነታችን ዘፍ ዘፍ እያለ "ለከርሞ አንተ ጣጣ" ተባብሎ መተላለፍ አልበቃ፤ የንዳጅ ዋጋ በተጨመረ፥ የረሀብ ሁኔታ ተከስቶ በተጋለጠ፥ ወዘተ በነዚህ ብቻ የካቲት ይደገማል ብሎ ዳር ቆሞ መጠበቅ አልረባ። ለተመረረ ሕዝብ የዘሌቄታ መፍትሔው ቆርጦ መነሳትና ጠላቱን በረዥሙና በመራራው ትግል ማደባየት ነው። ለዚህ ዓይነቱ አኩሪና አስከባሪ የጀግንነት ሙያ ሕዝባችን እንግዳ አይደለም። ማንስ ምስክር ጠይቆት! የካቲት ብዙ ያስታውሰናል፥ ለትግሉም ይቀሰቅሰናል፤ ሌላ መድኅን የለም፥ ሌላ መንገድ የለም አብሩ ቀጥሉ ይለናል!

ትግሉ ይቀጥላል!

በተራዘመ ሕዝባዊ ጦርነት ሰፊው ሕዝብ የማይቀረውን ድል ይቀዳጃል! !

እናቸንፋለን! !